# አል ቁድስ እና አባስ የዛሬ ዓመት

የዕምነት መሰረታቸውን በአንድ ፈጣሪ ላይ መስርተዋል ለሚባልላቸውና የነቢዩ ኢብራሂም (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይውረድ) ልጆች ለሚከተሉዋቸው ሶስቱ ታላላቅ ሃይማኖቶች- የአይሁድ እምነት፣ ክርስትና፣ እና እስልምና (ሞኖቴኢስቲክ ኤብረሃሚክ ሪሊጅንዝ) ሁሉ የዕምነታቸው መነሻና መድረሻ ያህል የምትቆጠረው ትንሽዬ ከተማ አል ቁድስ (እየሩሳሌም)በርግጥ ለሁሉም ቅድስት ከተማቸው መሆንዋ አስረጂ የማይሻ እውነት ነው፡፡ አይሁዶች የዳዊት ልጅ ሰሎሞን አስገነባው ብለው ለሚያምኑበትና የሰው ዘር በመጨረሻይቱ ቀን የሚሰበሰብበት፣ ቅድስተ ቅዱሳኑን በውስጥዋ የያዘች፣ የአይሁድ ጀግንነት መገለጫ፣ ለሚልዋት የከተሞች ሁሉ ከተማ እየሩሳሌም (አል ቁድስ) ያላቸው ፍቅርና ክብር ወደር የለውም። የፈጣሪን ስላሴነት ለሚመሰክሩ ክርስቲያኖች ከሶስትነቱ መታያ አንዱ የሆነው ብለው ለሚያምኑባቸው የእየሱስ ክርስቶስ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይውረድ) የመከራ ስርፋ፣ መቃብር መገኛ ሲሏት፣ ሙስሊሞቹም እንዲሁ ነቢዩ መሀመድ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይውረድ) ፈጣሪያቸው ዘንድ በክብር ቀርበው ዓማኝ ተከታዮቻቸው ሊያከብሩትና በየለቱም አምስት ጊዜ እንዲፈጽሙት በአብይነት የተጠቀሰውን ስግደት ትዕዛዝ ከፈጣሪ ይቀበሉ ዘንድ በውድቅት ወደ ሰማየሰማያት ያቀኑባት የአምልኮ ስፍራ (በይተል መቅዲስ) መገኛ ናትና ልዩ ቦታ መያዝዋ ይገባት እንደሁ እንጂ አይበዛባትም- እየሩሳሌም፡፡ ከተማይቱ ለየዕምነቶቹ ተከታዮች ዛሬም ድረስ የመንፈሳዊ፣ መለኮታዊ ውል ማሰሪያ፣ ብሎም የዓለማዊውም ህይወት ማውጠንጠኛ የእሽክርክሪቱ ዓይን ተደርጋ መታየትዋ እውነት ነው።

በኣዲስ ኪዳን እንደተነገረው ለሰው ልጆች ሁሉ ደግን ሊያደርግ ፈጣሪ የላከው፣ መልካምን የፈጸመው፣ ታሪኩ ባብዛኛው በአስቸጋሪ ውጣ ውረድ የተሞላው፣ ይሁንና ፍጻሜው በማያግባባው (እንደክርስቲያኖቹ ዕምነት ከሆነ የዚህ መልካም ሰው ህይወት በከሃዲዎች እጅ በማለፍዋ አሳዛኝ ፍጻሜ የተስተዋለበት፣ በሌላ ወገን ሙስሊሞች ለሰው ልጆች ምህረትን፣ ወደበጎ ይመለሱ ዘንድ ሃቅን የሰበከ መልክተኛውን አላህ (ፍፁም ጥራት ይገባው) በዚያ የመከራ ጊዜ ከሞት የታደገበት፣ እናም ፍጻሜው የዓለማት ጌታ ክብር የታየበት፣ ከፉን የተመኙና ሊፈጽሙም ያቀዱ ያፈሩበት እንደሆነ ያምናሉ) ብቻ ለሃይማኖቶቹ መለያየት ምክንያት በሆነው በዚህ ሰው ታሪክም ጭምር ሁሌም የትኩረት ማዕከል እንደሆነች አለች- እየሩሳሌም። ከተማይቱ እየሱስ (የአላህ ሰላም በእርሳቸው ላይ ይውረድ) ተዓምራትን ያደረጉባት፣ የእውነትን መልዕክት የሰበኩባት፣ ያይሁድ ሰዎች ይቀበሏቸው ሲገባ ይልቁንም ፈጣሪ የማይወደውን ሴራ የጠነሰሱባት፣ የዚያን የእውነት ሰው መከራ ያስተናገደች፣ እንደርሳቸው መከራ ሁሉ በተለያየ ጊዜ የተነሱ ኃያላን ያነሳቆልዋት ከመሆንዋ ጋር ተዳምሮ አንጀት መብላትዋ፣ ስለርስዋ እንደርስዋም ባይሆን እነርሱ እንዳሰቡት ሊታደጓት የሹ በርካቶችን ማፍራት የተቻላት ናት- አል ቁድስ (እየሩሳሌም)፡፡ ገነት በምድር የማለት ያህል መታየትዋም የዚሁ ጥግ የነካ ክብርዋ መገለጫ ነውና ለአል ቁድስ ይበዛ አይመስልም።

ቀድሞ፣ በይበልጥም በመሃከለኛው ዘመን ለነበሩ ነጋሲያን ይህችን ቅድስት ከተማ መቆጣጥር፣ በአፈርዋም ታምራትን ማድረግ ቦታ ነበራቸው። በርካቶችም ሊከፈልላት ይገባል ያሉትን ህይወታቸውን ሰውተውላታል። ይህን ስል ያን የከበረ ቦታ ዛሬ ላይ አጥታዋለች ማለቴ ግን ከቶ አይደለም፡፡ አውሮፓን ቆርጦ ወደመሃከለኛው ምስራቅ ዘምቶ የነበረው የዚያኔው አውሮፓዊ የመስቀል ዘማች የልጅ ልጅ ዛሬ ላይ መለኮታዊ ዋጋዋ በያኔው ብርታት ባይታየውም ፖለቲከኛው አውሮፓዊና አሜሪካዊ የከተማዋን መጻዒ ዕድል በተመለከተ በየተገኘው ኣጋጣሚ ሁሉ ማንሳቱን ለመግለፅ አስረጂ መቁጠር አያሻም።

በወርሃ ጥቅምት 24, 1945 እንደፈረንጆቹ አቆጣጠር የተባበሩት መንግስታት ሲቋቋም ያኔ ፍልስጤም አደራውን በ1922 ከመንግስታቱ ማህበር ተቀበልኩ ባለችው በታላቋ ብሪጣንያ እጅ ነበረች። ዘመን በዘመን ላይ ሲደራረብ ከደጅም ከውስጥ እየገፋ የሄደውን ዓመጻ መቋቋም የከበደው የብሪጣንያ መንግስት የፍልስጤምን ጉዳይ ለተባበሩት መንግስታት አቅርቦ እንዲጤን አድርጓል። እዚህ ላይ

በፍልስጤም ይታይ የነበረው፣ አሁን አሁን ከስምንት ሜትሩ የድንጋይ  አጥር በኋላ ቀንሷል: የሽብር ጥቃት በኣይሁድ ነዋሪዎችና መሪዎቻቸው እጅ በስፋት ይፈጸም እንደነበር ማስታወስም ተገቢ ነው።

የፍልስጤምን ጉዳይ እንዲመረምር ተዛማጅ ጥያቄዎችንም እንዲያጤንና  ለተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባዔ የመፍትሄ ሃሳብ ያቀርብ ዘንድ የተዋቀረው ልዩ ኮሚቴ ያይሁድ ድርጅቶችን ትብብርና ዕገዛ ሲያገኝ ባንጻሩ የፍልስጤም ጉዳይን እወክላለሁ ያለው የዓረብ ወገን ተሳትፎውም ሆነ ትብብሩ አንሶ የተባበሩት መንግስታቱ ኮሚቴም ሁለት ሃሳብ ይዞ ባቋሙ ተከፍሎ ቀርቧል። በዚሁ ከአንድ መድረስ ባልተቻለበት ሂደት ያብላጫውን ይሁንታ አገኘ የተባለው ወገን ለፍልስጤማዊያኑና ላይሁዶች የሚሆን የተለያየ ግዛትን ሲመክር ባንጻሩ አወዛጋቢ ቅድስት ከተማይቱ በተባበሩት መንግስታት ስር ትቆይ ዘንድ መምከሩም ቢበዛ የሰባት አስርት ዓመታት ታሪክ ነው። ደጋፊም ነቃፊም ያላጣውን ይህን ሃሳብ ኢትዮጲያ በድምጸ ተዓቅቦ ማለፍዋ በወቅቱ የነበረው ሰሎሞናዊ ስርወመንግስት የዘር ሃረጌ ይመዘዝባታል ላላት ያይሁድ ሃገር እስራኤል (ከሚሊየን የሚልቁ አረብ እስራኤላዊያን መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ) አሊያም ዙሪያዋን ለከበቡ ሙስሊም ጎረበቶችዋ ያለማድላቱ ምልክት ተደርጎ ሊታሰብ ይችላል።

በወቅቱ ክፍፍሉን ተከትሎ ለሚገጥመው የዕምነት ቦታዎች እሰጥ አገባ ምላሽ ይሆን ታስቦም  የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ውሳኔ በማምለኪያ ስርፋዎች አንጻር ምንም ገደብ እንደማይኖር ቢያትትም እስራኤል በሙስሊሞቹ ማምለኪያ መገኘትን በጄ የምትለው አመጽ የማስነሳት ፍላጎት ብዙም አይታይባቸውም፣ ቢሞክሩም ለመቆጣጠር አያስቸግሩም ለምትላቸው አረጋውያን መሆኑን ላጤነ እስራኤል የያኔውን ስምምነት አሁንም ድረስ እንደዋዛ ከሚጣሱት የተባበሩት መንግስታት  ውሳኔዎች (ሬዘሉሽንዝ) የተለየ ቦታ ሰጥታው እንደማታውቅ ማሳያ ሊሆን ግን ይቻለዋል፡፡ የኢራኑ እስላማዊ አብዮት መሪ አያቶላህ ሮህላ ሆሜይኒ (አፈሩን ገለባ ያድርግላቸውና) በዚህች ቅድስት ከተማ አንጻር ያስተላልፉት ሃይማኖታዊ ምክርና የረመዳንን ወር የመጨረሻ ዕለተ አርብ የአልቁድስ ቀን ሲሉ መሰየማቸውም ለይሁዳዊያኑ ራስ ምታት መሆኑ አመት አልፎ አመት በተተካ ቁጥር ሲብስ እንጂ ሲቀል አለመታየቱም ለእየሩሳሌም ትኩረት ሳቢነት አስተዋጽዖው አሌ አይባልም፡፡ የዕስራኤልን የቅርብ ጊዜ ፖለቲካ ፍጹም ጽንፍ እንዲይዝ በማድረጋቸው ስማቸው በግቢም በደጅም ተደጋግሞ የሚነሳው አቪግዶር ሊበርመን የከተማይቱ አይከፋፈሌነት፣ የፍጹም ይሁዲዎች ሃገር ዋና መዲናነት አቋምም እንዲሁ ለእየሩሳሌም ጉዳይ ያው ግብዓት ናችው፡፡

የ አል ቁድስ እየሩሳለም ጉዳይ የረባ መረጋጋት ባልታየበት፣ አረብ ነዋሪዎቿ በሕገ ወጥ ግንባታ ስም በሚፈናቀሉበት፣ እስራኤላዊያኑ አይሁዳዊ ይዘቷን በሚያጠናክሩበት በዚህ ጊዜ ነው ታዲያ ሰሞኑን በተለመደውና በየኣመቱ ከመስከረም ሶስተኛው ማክሰኞ ጀምሮ እስከ ገና በዓል በሚዘልቀው የሶስት ወራት ያህል ቆይታ (የተለየ ነገር ከገጠመ ካውዳመት በኋላም ሊቀጥል ይችላል) እና ሁሉም የልቡን ብሶት በሚናገርበት የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ፊት ቀርበው ማህሙድ አባስ (አቡ ማዝን) ድርጅታቸው የፍልስጤም ነፃ አውጪ ግንባር ያለውን የታዛቢነት መቀመጫ በመጠቀም  ለተሰብሳቢዎች ንግግር ያደረጉት።  በዚሁ ወቅትም እስራኤል በጋዛ ነዋሪዎች ላይ የጣለችው ኢፍታዊ የምድር፣ የባህር፣ እና ያየር ማዕቀብ በነዋሪዎች ላይ ያስከተለው አጠቃላይ ስቃይና መከራ፣ ይህም የፈጠረው የስራ አጥነት ችግር ይቆም ዘንድ እስራኤልን ያሳሰቡት፣ በኃይል ከተቆጣጠረቻቸው የፍልስጤምና አረብ ግዛቶች እንድትወጣ የወተወቱት፣ ለፈራረሱት የጋዛ መንደሮች ዳግም ግንባታ አለም አቀፉ ህብረተሰብ ቢሊየኖች ቢያቀርብም በዚህም አንፃር ግንባታ ለማካሄድ ችግር እንደገጠማቸውም ያማረሩት። በሌላ ወገን ሰብዓዊ ዕርዳታ ለማድረግ የተንቀሳቀሰው ቡድን በእስራኤል ኃይሎች የተፈፀመበትን ጥቃት የሚያጣራ እውነት አፈላላጊ ቡድን መዋቀሩን አወድሰው ምላሹን ለማወቅ እንደሚሹም አስረድተዋል፡፡ ስለ ሰላም ሲባልም በእስራኤል ማረሚያ ቤቶች የታጨቁ ፍልስጤማዊያን ወገኖቻቸው ይፈቱ ዘንድም ጠይቀዋል፣ የአፓርታይድ ግድግዳውንም ኮንነዋል ፕሬዝዳንቱ። የሰፈራ እንቅስቀሴዎችን መቆም ከሰላም ማግኘት ጋር በማቆራኘት ምንም እንኳ በዚያች ሃገር እርምጃዎች ታሪካዊ ኢፍትሃዊ ግፍና መከራን ቢቀበሉም የቆሰለ እጃቸው የወይራ ዝንጣፊ ይዞ ለመቅረብ ያለመቦዘኑን፣ ዛሬም በሰላምና

መከባበር ተቻችለው ጎን ለጎን የሚኖሩ ነፃ የፍልስጤምና ያይሁድ ሃገራት ለመመስረት እንደሚተጉ፣ ለተጀመረው የሰላም ድርድር ስኬትም ሁሉን ነገር እንደሚያደርጉ እንደሁልጊዘው ቃል ገብተዋል- ለነጻይቱ ፍልስጤም ያመት ቀጠሮ እንደማለት።

ይህች ይሁንታዋን አጥብቀው የሚሸዋት ሃገር እስራኤል ስትመሰረት ገና ያስራሶስት ዓመት ታዳጊ የነበሩትና እንደርሳቸው ሁሉ ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ እያደገች እየሰፋች እንጂ እንደለሎች ባልንጀሮችዋ ባለችበት ላልተወሰነችው ሃገር እስራኤል ንግግሩ የተለየ ነገርያመጣል ማለት ይበልጡንም የስልጣን ዕርካቡን ጨብጦ ካለው ጥምር መንግስት አንጻር ሲገመገም ጉዳዩ የቀልድ ያህል መሆኑ እርግጥ ነው። ምናልባት የተባበሩት መንግስታት የድምጽወምስል ክምችት ክፍልን  በመረጃነት ለሚጠቀሙ ይረባ እንደሁ እንጂ እርሳቸው አማላይ አድርገው እንዳቀረቡት አይነት የዛሬ አመት ነጻይቱ የፍልስጤም መንግስት ተቋቁማ የቅድስት ከተማ እየሩሳሌምም ምስራቃዊ ክፍል ርዕሰ መዲናዋ ሲሆን ማየት የዘበት ያህል ነው፡፡ በሃያአንደኛው ክፍለዘመን እንደኋለኛው ጊዜ ጥቂት ጽዮናዊያን እንዳሻቸው ለሚያንገላቱት ፍልስጤማዊ ሕዝባቸው ተስፋን ይሰንቃል ማለትም የዚያን ሕዝብ ስሜት አቅልሎ ማየት ይሆናል።

የ 1994 ኖቤል ሽልማት አሸናፊው ያሰር ኣራፋት (አፈሩን ገለባ ያድርግላቸውና) ባንድ ወቅት ነጻይቱን የፍልስጤም መንግስት ለማወጅ ቅድሚያ ዲፕሎማሲያዊ ማግባቢያ ከኃያላኑ ሃገራት ለማሰባሰብ፣ ወዲያውም የፖለቲካ ትኩሳቱን ለመገምገም ይርዳ እንደሁ ሲሉ ወደተለያዩ ያለም መዲናዎች ጉዞ ማድረግን ባሰቡ ጊዜ በብርቱ የዛቱባቸው፣ የኋላ ኋላም ከታገቱባት ራማላህ ከተማም ነጻነትን ቢሹ መመለሻ የለሽ የአንድ ጊዜ ቲኬት ይቆርጡ ዘንድ ያስጠነቀቋቸው የቴል አቪቭ ሹማምንት፣ ኣራፋት በፓሪስ ሆስፒታል ድንገት ዜና ህልፈታቸው ሲነገር ከእንግዲህ ስለሰላም ልናናግራቸው የሚቻለን ተተኪ ሲሉ እስራኤላዊያን ፖለቲከኞች ላሞካሹዋቸው ሰው ማህሙድ ኣባስ (ኣቡ ማዝን) የታሪክ ከወጪ ቀሪ ዝና መዳኅስ፣ ማማር፣ ባለተራዎቹ ቤንጃሚን ናታንያሁ፣ ኣቪግዶር ሊበርመንም ሆኑ፣ ኣቫዲያ ዮሴፍ ይዋትታሉ ማለትም እንዲሁ የዚያን አካባቢ ስስ የፖለቲካ አወራረድ በቸልታ እንደማየት ሊቆጠር ይችላል፡፡ አንድ አመት ሙሉ ድርድር መፍትሄ ለማፈላለጊያ ያንሳል ማለት ባይዳዳኝም አሁን ነገሮች ያሉበትን ሁናቴ ላጤነ የእስራኤል ፍልስጤም ያስርት አመታት ግጭት ከማብቂያው ደረሰ ለማለት ግን አያስደፍርም ባይ ነኝ፡፡

ቀን አልፎ ቀን ሲተካ እስራኤል የምትቆጣጠራቸው ግዛቶች መስፋት፣ የማህሙድ አባስም ሕዝብ የሚመሩበት የፈቃድ  ጊዜ ሁለቱም ከተወሰነላቸው ገደብ ያለፉ፣ በማለፍም ላይ ያሉ መሆኑን እያስታወስን መጪውን እንጠብቅ- ሰላም።

**መ. ሷልህ**